# የት ደርሰናል? የሀገራችንና የአካባቢው ሁኔታ

አሬቲ ተካ

ትግሉ ፈሩን ሳይለቅ ወድ ድል እንዲያመራ ከተፈለገ የሀገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ በስርዓት መግምገምና የአካባቢና ዓለም አቀፍ ሁኔታንም ማገናዘብ ያስፈልጋል። ተጨባጭ ሁኔታን መመርመር ማለትም ሁኔታን በግልቡ ማየትና ለድምዳሜም መገስገስ ማለት አይደለም። ወያኔ ሶማሊያ ገብቶ ወረራ በማካሄዱ አሜሪካንን አስደስቷልና ማንም አይነቀንቀው፣ተቃዋሚዎች ተከፋፍለዋልና ወያኔ ከቀውሱ ወጥቷል፣ ቄሱም ዝም መፅሀፉም ዝም ነውና በሀገር ቤት ምንም ጉልህ ተቃውሞ አይታይም፣ በቃ አበቃልን ብለው በቀቢፀ ተስፋ የሚናጡ ሁሉ ተጨባጩን ሁኔታ በጥሞና መገምገም ስላቃተቸው ነው። ግዢው ክፍል ሁኔታዎችን በሚገባ መመዘን ካቃተው በራሱ መደናገር ራሱን ለውድቀት ያዘጋጃል። የሕዝብ ጎራ ደግሞ ተጨባጩን ሁኔታ በትክክል ማየት ከተሳነው በዕቅዱ ይሳሳታል፣ በተስፋ መቁረጥ ይዋጣል፣ ጠላት ወዳጅ መለየት ያቅተዋል፣ ወደ እጅ መስጠትም ሊያመራ ይችላል። ጎሩን አየህና ገደሉን ሳታይም ሊከተል ይችላል።

በአሁኑ ጊዜ ዓለም እንደበፊቱ በካፒታሊስት አሜሪካና በሶቭየቱ ጎራ የተከፋፈለች ሳትሆን አሜሪካ በብቸኛነት ሊነዳት የሚጥርባት ብትሆንም ከአሜሪካ በመፃረር ሌላ የተሻለ ዓለም አለ / መፍጠርም ይቻላል የሚሉ ክፍሎች እየተጠናከሩ የመጡባት ዓለም ናት። በአሜሪካና በምዕራባውያን ላይ የተነሱ አክራሪ ሀይማኖታዊ ቡድኖች ያሉ ሲሆን የሕዝብን መብት ማስከበር አንፃር ደግሞ ፀረ ብዝበዛ ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆኑ ክፍሎችም እየበረከቱ ያሉ ናቸው። ይህ በተለይ በአሁኑ ጊዜ በደቡብ አሜሪካ እየታየ ነው። ስለዚህም ለአሜሪካ መንበርከክ ሳይሆን መታገል መቻሉንም ጠቋሚ ክስተቶች መኖራቸውም መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በሀገራችን ሁኔታ ስናየው ደግሞ ሊካድ የማይችለው ሀቅ አሜሪካ ከወያኔ ጎን መሰለፉ ነው። የእንግሊዙ ብሌይር አልፎ አልፎ ወዳጄ ነው ይለው የነበረውን መለስን ቢተችም ከመጋረጃው በስተጀርባ ግን የወያኔ አጋር መሆኑ የሚደበቅ አልሆነም። የአሜሪካ ወታደሮች በኢትዮጵያ መሬት ሰፍረዋል። አሜሪካ ወያኔን ለመከላከል ፀረ ሽምቅ ተዋጊ ጦር በብላቴን አሰልጥኗል፣ እያሰለጠነም ነው። አሜሪካ በገንዘብና በዲፕሎማሲው መስክ ለመለስ ሙሉ ድጋፍን እየሰጠ ነው። የዚህ አንደምታ በሚገባ ተመርምሮ ከትግል አንፃር ምን አቅዋምና እርምጃን እንደሚጠይቅ መወሰን ያለበት ነው። የሕዝብ ጎራ ከዚህ በመነሳት ደግሞ ማንን በወዳጅነት ይዞ ከትግሉ ጎን ማሰለፍ እንዳለበት ማወቅም አለበት። አሜሪካንን በመማፀን ለሀገር ሰቆቃ ምላሽ እገኛለሁ ማለት ሰው መስሎኝ ደንጊያን ቆነጠጥኩ መሆኑ የሚጠበቅ ነው።

ኢትዮጵያ ከታሪኳ፣ የአባይ ምንጭ በመሆኗ፣ ባለችበት አካባቢ ተፈላጊነት÷ከሕዝቧ ብዛት የተነሳ፣ በአፍሪካ ካላት ቦታና ሚና አንፃር ባዕዳን ለደግም ለክፉም ዓይናቸውን ጥለው በበጎም በክፉም እየተረባረቡባት ቆይተዋል። ይህን በሚገባ ተገንዝቦ ተገቢውን የውጭ ፖሊሲ የሚከተል መንግስት ለማግኘት ግን አልታደለችም። ከዚህም የተነሳ በደልና ጉዳትን መሸከም የግድ ሆኖባት ቆይቷል። በተለይም ህልውናዋን የሚጠላ ቡድን በስልጣን በመሰየሙ ደግሞ ደጋግሞ ለጉዳት አጋልጧታል ማለትም ይቻላል። ወያኔ ሶማሊያን በመውረሩ የተነሳ በአካባቢው ችግር መፈጠሩ የሚታይ ነው። ከሻዕቢያ ጋር እየተቀራረበና እያደር ከአሜሪካ ደበልጥ እየተቃቀረ የመጣው የሱዳን መንግስት ወያኔ የአሜሪካ ቡችላ ሆኖ ሶማሊያን መውረሩን ከመቃወሙ በተጨማሪ የሱዳን መሪ ኦማር በሺር የአፍሪካ ድርጅት ሊቀመንበር ሆኖ ለመሰየም ሲጥር መለስ አለመደገፉ አስቆጥቶታል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሻዕቢያ ከሱዳን ጋር በጣም እየተወዳጀ መምጣቱ ሌላ ችግር ሆኖ የወያኔና ሱዳንን ችግር በመጠኑም ቢሆን አሻክሯል ሲሉ ታዛቢዎች ዘግበዋል። ሱዳን ግን በዳርፉር ብቻ ሳይሆን ሰላም መሰረትኩበት ባለው በደቡብ ሱዳንም ቢሆንም ችግር እየተፈጠረበት ነውና ከወያኔ ጋረ ጠብ መክፈቱ የሚያዋጣው አይመስልም። በጅቡቲ የአሜሪካ ጦር ሰፍሮ ቢገኝም ከአረብ ሀገሮች ጋር የተያየዘው የጅቡቲው መሪ ኦማር ገሌህ የወያኔን የሶማሌ ወረራ መቃወም ግዴታ ሆኖበታል። ኦማር ገሌህ በአሁኑ ወቅት ከሻዕቢያ ጋር ተወዳጅቶ መገኘቱ ደግሞ የአደባባይ ምስጢር ሲሆን በርካታ የኦነግና የኦጋዴን ሽምቅ ተዋጊዎችም ቢሆኑ በግዛቱ አልፈው ወደ ኢትዮጵያም ሶማሊያም መጓጓዛቸው የሚካድ አይደለም። በጅቡቲ ራሱ የአፋር ተቃዋሚዎች/ ፍሩድ በሚባል የሚታወቁት/ የሰላም ትግል በሚል የተወሰነ ሙከራ አድርገው ይህ በመክሸፉ ዳግም ትጥቅ ትግል ጀምረዋል። የድርጅቱ መሪዎችና ዛሬ የሞቱት እነ አህመድ ዲኒ ከአገዛዙ ጋር በሰላም በመተባበር ወደ ፊት እንሄዳለን ያሉት ስላልሰራና አገዛዙ ምንም ባለመለወጡ የአፋሮች የትጥቅ እንቅስቃሴ መጀመሩ የግድ ሆኗል።

ወያኔ በሶማሊያ ገብቶ መውጫው ግን ጠፍቶታል። ሶማሊያ ውስጥ አየል ብሎ የመጣው የአክራሪ እስላማውያን እንቅስቃሴ ከሞቃዲሾ ቢባረርም እንደገና እየተደራጀና ትግሉንም እያጠናከረ በመሆኑና ወያኔ የደገፈው የአብዱላሂ ዩሱፍ /የዳሮድ ጎሳ ተወላጅ/ በቂ ድጋፍ ስለሌለው በቦታው ለማቆየት የወያኔ ጦር በቦታው ለረጅም ጊዜ በሶማሊያ መቆየት እንዳለበት ግልፅ ነው። ምክንያቱም በሶማሊያ ቋሚ ማዕከላዊ መንግስት ይቋቋማል ብሎ መገመት ዘበት መሆኑ ክርክር ጠያቂ አይደለምና ነው። የሶማሊያ ዋና ችግር የጎሳ ብጥብጥ መስፈኑ ነውና ለዚህ ወያኔያዊ መርዝ መፍትሄ ካልተገኘ በሶማሊያ ሰላም ከቶም አይሰፍንም። መለስ ግን ሊወጣ ከማይችለው ማጥ ገብቷል ብንል ማጋነን አይሆንም። ይህ ወረራ ግን ለመለስ አገዛዝ የተወሰነ ትርፍ አስገኝቶታል። በሀገር ውስጥ ሕዝቡ ለወያኔ አስመሳይ ሀገር ወዳድነት ጆሮ ባለመስጠቱ የመለስ ቡድን የተመኘውን ድጋፍ አላገኘም። ይህ የሀገር ቤቱ ኪሳራ ግን ከአሜሪካ ሊያገኝ በቻለው የገንዘብና መሳሪያ ድጋፍ በመጠኑም ቢሆን ተክሷል። የሶማሊያ ወረራ በአሜሪካና የሶማሌ የጦር አበጋዞች የተዘጋጀ እንጂና በእነ ባጫ ዳባሌ የተነደፈ ካለመሆኑ ሌላ የአሜሪካ ልዩ ጦር ወታደሮችም ከወራሪው ጦር ጋር ተደባልቀው መዋጋታቸው ተጋልጧል። በዚህ የቅጥረኛ ስራው መለስ ዜናዊ ተጠናክሯል የሚሉ የአንድ ጎን ዕይታ ያላቸው ብቻ መሆናቸው ግልፅ ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የወረራው መዘዝ ገና እየጀመረ እንጂ እየተጠናቀቀ አይደለም። የከሰረ አገዛዝ ደግሞ በገንዘብ አቅም ረጅም ዕድሜን አይገዛም። በሌላ በኩል ደግሞ በሶማሊያ መሬት ሊካሄድ በተጠበቀው ውጊያ የራሳቸውን ግብ ሊመቱ የፈለጉት ክፍሎች ያሰቡት አልተሳካላቸውም። የኦነግና የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባሮች ጉዳት ደርሶባቸዋል የተባለውም በደፈናው የሚካድ አይደለም። ወያኔ ያዝኳቸው ያላቸው የኤርትራ ጄኔራሎች ግን የውሀ ሽታ ሆነዋል። በአጭሩ የሶማሊያው ቀውስ ቀጣይ ይሆናል ማለት እንችላለን።

ይህ በዚህ እንዳለ ግን ቢገባ መመርመር ያለበት ጉዳይ በአፍሪቃ ቀንድ በሚባለው አካባቢ አሜሪካ በሩቅ ሳይሆን በቅርብ ማለትም ወታደርም ልኮ አለሁ አለሁ እያለና የራሱን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በስፋት እየተንቀሳቀሰ ነው። በዚህም መሰረት የመለስን አገዛዝ ለመደገፍ በሚል በብላቴን ፀረ ሽምቅ ተዋጊ ጦር አሰልጥነውለታል። የሻዕቢያንም በድንበር የጦር አሰላለፍ/ ክምችት በተመለከተ አሜሪካ የሳተላይት የስለላ ፎቶግራፎችን ለወያኔ መስጠቷ ታውቋል። ይህ የአሜሪካ ጣልቃ ገብነት ከህዝብ ትግል አንፃር ሊያስከትል የሚችለው መዘዝ በሚገባ መታየት ያለበት ነው። በኬንያ፤ በዩጋንዳ ወዘተ ያሉት ቀውሶች ራሳቸው በዚህ የአሜሪካ ፖሊሲ መሰረት የሚካሄደው ሁሉ አሉታዊ መሆናቸውን ማመልከታቸውን ያረጋግጣል። ከዚህ ሌላ ግን ወደ ተጨባጩ የሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ የመለስ አገዛዝ ይዘትና ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን በተመለከተ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።

- በአጠቃላይ የፖለቲካው ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ የስልጣን ጥያቄ ቢሆንም ፖለቲካ ስንል ትግል ዋናው ጉዳይ የህዝብን ሁኔታ የሚመለከት መሆኑ መሳት የሌለበት ጉዳይ ነው። የሕዝብ ኑሮና ሁኔታ ቅድሚያ ከተሰጠው ደግሞ የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ላይ የመጣ ቁጣ መሆኑን እንገነዘባለን። ዋሾዎቹ የዓለም ባንክና ሰላዩ ፖል ሄንዚ ኤኮኖሚው አደገ ተመነደገ ብለው የሚቧርቁትን ወደ ጎን ብንተወው ሀቁ የሚያሳየው በሀገራችን ድህነት ስር ሰዶ መክፋቱን፤ የጤፍና ሌሎች ምግቦች ዋጋ ባለፈው ዓመት ብቻ ሀያ ሰባት በመቶ እጅ መጨመሩን፤ የትምህርትና የጤና ይዞታ መበላሸቱን፤ ከድህነት ጠርዝ በታች የሚኖረው ህዝብ ወደ ስድሳ በመቶ መጠጋቱን፤ በአዲስ አበባ ራሱ ተገቢ መጠለያ ያጣው ህዝብ ቁጥር ከግማሽ ሚሊዮን ማለፉን፤ ዛሬም ቢሆን በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ መራቡንና አርሶ አደሩ ህዝብም በችጋር መጠበሱን እናያለን። ከሕዝብ አንፃር ያደገ ኤኮኖሚ የለም። የሀገሪቷ አንጡራ ሀብት ወደ ውጭ ወይም ወደ ክልል አንድ እየተጓጓዘ መሆኑንም መካድ ከቶ አይቻልም። ሙስናና ዝርፊያ፤ ዋልጌነትም ተስፋፍቷል። በሰብዓዊ መብት ደረጃ ደግሞ የዛሬው ካለፈው ዓመት እየከፋና ህዝብ እየታሳረ፤ ታስሮ እየተገረፈና እየተሰቃየ፤ በአጠቃላይም ፍትህ እየተረገጠች አለች እንጂ የተሻሻለ ሁኔታ የለም።
- የመለስ አገዛዝ በአሁኑ ወቅት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ደክሟል እንጂ በላይ ላይ ሊታይ እንደሚችለው አልተጠናከረም። በግራ ቀኙ ገነዘብ እየረጨና በተለይም በውጭ ሀገር ያሉትን በንግድ ፈቃድና በመሬት መመራት እየደለለ ተቃውሞን ሊያረግብ ቢጥርም ለውድቀቱና ለድክመቱ ዋና ምክንያት የሆነው የሕዝብ እምቢታና ተቃውሞ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ሕዝብ እንደወትሮው አልገዛም ብሎ ከተነሳ የአገዛዙ ውድቀት መጀመሩን አስረግጦ ማቅረብ ይቻላል። የነገ ቀን ተመን ወይም የጊዜ ቀጠሮ ማድረግ ቢሳንም አገዛዙ ወደ ውድቀቱ መጓዝ መጀመሩ ግን የሚጠረጠር አይደለም። ውስጡ ደበልጥ ላልቷል፤የሚከዱት በዝተዋል፤ ምንጠራውን በሰራዊቱም ሳይቀር ማካሄድ ተገዷል። የጭፍን ጉልበት አገዛዝ ዕድሜ ደግሞ ረጅም አለመሆኑ ተደጋግሞ የታየ ነው።
- በአሁኑ ወቅት በግንቦት 97ኙ ምርጫ ውጤት የደነገጠው ወያኔ ዋነ ትኩረቱ የሀገሪቷን ሀብት ወደ ውጭ ሀገር ባንኮቸ ማጓጓዝ ላይ መሆኑ ሲታይ በሌላ በኩል ከሻዕቢያ በመጣላቱ ተወት አድርጎት የነበረውን የትግራይ ትግረኚ ነፃ ሀገር ምስረታ ዕቅዱን ደግም ነፍስ ሊዘራበት ተነስቷል። ይህ ትግራይን ገንጥሎ ከክርሰቲያኑ ወይም ከበሳዩ ኤርትራ ክፍል ማዋሀድ የሚል ጊዜን ያስቆጠረ ህልም የመለስ ተወዳጅ ፍላሳት ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ሆኖም በሻዕቢያና በወያኔ መሀል በተፈጠረው ግጭት የተነሳ ይህ ዕቅድ ቢደናቀፍም ዛሬ አመቺ ሁኔታ አለ ተብሎ በጥንቃቄና በምስጢር እየተገፋበት ነው። በአንድ በኩል የትግራይን አቅም ግንባታ ተብሎ በተነደፈውና ይፋ ባልሆነው ሰነድ አማካኝነት ትግራይን መገንባቱና ለነፃ ሀገርነትም ማዘገጀቱ ሲገፋበት በሌላ በኩል ደግሞ በኤርትራ ውስጥ ለዚሁ ዕቅድ ደጋፊ የሆኑና ሻዕቢያን ተኪ የሚሆኑ ሃይሎችን ማዘጋጀት ነው። በዚህም መሰረት የኤርትራ ተቃዋሚዎችን ሰብስቦ የነበረው ህብረት/ኢዲኤ/ ለሁለት ተከፍሎ ብሎክ አንድ የተባለው ኬሌሎቹ ተለይቶ ከወያኔ ተቀራርቦ መስራት ጀምሯል ተብሏል። ይህ የመገንጠል የመገነጣጠል ዕቅድ ይሳካ አይሳካ ወያኔ ቀውጢ ቀን እንደመጣበት መገንዘቡን ያረጋግጣል።
- ሁኔታው ለውጠን አርግዞ ባለበት አዋለጅ ሊሆን የሚገባው የተቃዋሚ ደርጅቶች ህብረት በቦታው ሊከሰት ባለመቻሉ የሕዝብ ትግል መጓተቱ አልቀረም። እስካሁን የተሞከሩት ህብረቶች እየተጠናከሩ ሳይሆን ለችግረም ምክንያት እየሆኑ በመምጣታቸው የሕዝብ ትግል አለመረ በወያኔ ሊጠቃ ችሏል። ይህን ሁኔታ በምን መንገድ አሰወግዶ ወደፊት ወደ ድል ልንጓዝ እንችላለን የሚለውን ጥያቄ በቀጣዩ ፅሁፌ ልምልስ እሞክራለሁ።

<u>**ይቀጥላል**</u>

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com